# በየካቲት 12 የመሰናዶ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ


በ

አቤል ገ/ኪዳን


የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት

ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ


አዲስ አበባ

ሰኔ 2001 ዓ.ም

# በየካቲት 12 የመሰናዶ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ


በ

አቤል ገ/ኪዳን


አማካሪ

አቶ ተሻገር አስማረ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት

ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ


አዲስ አበባ

ሰኔ 2001 ዓ.ም

## አበርክቶ

ይህ ጥናት በምርጫ ወቅት በጥይት ተመትታ ለሞተችው አክስቴ ክብነሽ መልኬ እና በህመም ለተለየችኝ አክስቴ ወርቅነሽ ዳርጌ መታሰቢያ ይሁንልኝ፡፡

## ምስጋና

ለወደደኝ፣ ለመረጠኝ እና ላከበረኝ የድንግል ማርያም ልጅ ከሁሉም የበለጠ እና የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በማንኛውም ቦታ እና ሁኔታ ከጎኔ ላተለየችኝ እናቴ ለወ/ሮ የሺ ለማ እንዲሁም ለቤተሰቦቼ የማቀርበው ምስጋና ልባዊ ነው፡፡

የእግዚአብሄርን ስጦታ ስታቀብሉኝ ለኖራችሁት ለ ኮምፓሽን ኢትዮጵያ እና ለመሰረተ ሀይማኖት ሰ/ት/ቤት ታላቅ የሆነ አክብሮት አለኝ፡

በእውነተኛ ፍቅር ከጎኔ ለቆማችሁት ጓደኞቼ የማቀርበው ምስጋናም ቀላል አይደለም፡፡

በጥናቱ ወቅት በጥንቃቄ በማረም እና ጠቃሚ አስተያየት በመስጠት ይህን ጽሁፍ እንዳዘጋጅ የረዱኝ አማካሪዬ አቶ ተሸገር አስማረ ሳላመሰግን አላልፍም፡፡

ጥናቱን በገንዘብ የደገፉኝ አክስቴ አረጋሽ ይመር እና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል በመጻፍ ያገዘችኝ ወ/ሮ ነጻነት ሽኩሪ ታላቅ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

## ማውጫ


ገጽ

ምስጋና……………………………………………………………………………………………i
አበርክቶ…………………………………………………………………………………………ii
ማውጫ………………………………………………………………………………………… iii
አጠቃሎ………………………………………………………………………………………..

ምእራፍ አንድ

1. መግቢያ…………………………………………………………………………………
   1.1. የጥናቱ ዳራ……………………………………………………………………1
   1.2. የጥናቱ አላማ…………………………………………………………………2
   1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ………………………………………………………………2
   1.4. የጥናቱ ክልል…………………………………………………………………3
   1.5. የአጠናን ዘዴ…………………………………………………………………3

ምእራፍ ሁለት

2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት……………………………………………………………………..5
   2.1. ንባብ ምንድን ነው?……………………………………………………………5
   2.2. የንባብ ጠቀሜታ………………………………………………………………5
   2.3. የንባብ አይነቶች……………………………………………………………..6
      2.3.1. ተግባራዊ ንባብ/Functional reading/……………………………………6
      2.3.2. የማሻሻል ንባብ /developmental reading/……………………………...7
      2.3.3. የመዝናኛ ንባብ /recreational reading/…………………………………7
   2.4. የንባብ ደረጃዎች………………………………………………………………7
      2.4.1. እማሬያዊ ንባብ /reading for Literal meaning/………………………….7
      2.4.2. ፍካሬያዊ ንባብ /reading to make inference/…………………………..8
      2.4.3. የምዘና ንባብ / reading to Evaluate/……………………………………8
   2.5 የአነባበብ ቴክኒኮች(ስልቶች)…………………………………………………....8
      2.5.1 የአሰሳ ንባብ /scanning……………………………………………………8
      2.5.2 ግርፍ ንባብ /Skimming……………………………………………………..9
      2.5.3 ሰፊ ንባብ /Extensive reading……………………………………………..9
      2.5.4 ጥቅል ንባብ /Intensive reading……………………………………………9
   2.6 የንባብ ልማድ እንዲዳብር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ አካላት…………………………..9
      2.6.1 ቤተሰብ……………………………………………………………………10
      2.6.2 ማህበረሰብ…………………………………………………………………..10
      2.6.3 ትምህርት ቤት……………………………………………………………...10
      2.6.4 ባህል………………………………………………………………….…..11
      2.6.5. ግላዊ ባህሪ………………………………………………………………11
   2.7. ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች……………………………………………..11
   2.8. የንባብ ምርጫ………………………………………………………………...12
   2.9. ጠቃሚ የአነባበብ ቴክኒኮች……………………………………………………13
      2.9.1. ስሜትን መረዳት /Sensitizing/……………………………………………13
      2.9.2. የንባብ ፍጥነትን ማሻሻል…………………………………………………13

2.9.3. የአሰሳ ንባብ /Scanning/ መለማመድ……………………………………………..13
2.10. የተሳሳቱ የአነባበብ ቴክኒኮች……………………………………………………...14
2.10.1. ድምጽ እያሰሙ ማንበብ /Subvocalizing/…………………………………………14
2.10.2. በጣት መጠቆም /Finger pointing/………………………………………………14
2.10.3. ወደኋላ መመለስ /Regression/…………………………………………………14

## ምእራፍ ሶስት

3. የጥናቱ ውጤት ትንተና……………………………………………………………………..15
3.1. የተማሪዎች ምላሽ ትንተና………………………………………………………………15
3.1.1. ትምህርት ነክ ያልሆኑ ፅሁፎችን የማንበብ ልምድን አስመልክቶ
ተማሪዎች የሠጡት ምላሽ ትንተና…………………………………………………16
3.1.2. የንባብ ምርጫን አስመልክቶ የተማሪዎች ምላሽ ትንተና……………………………..20
3.1.3. ተማሪዎች ትምህርት ነክ ስላልሆኑ ጽሁፎች ያላቸውን ግንዛቤ ትንተና…………….21
3.1.4. የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች የማንበብ ልምድ
ላይ አስተዋጽኦ ያደረጉ አካላት……………………………………………………...22
3.2. የየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት የቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ ትንተና………………23
3.2.1. ንባብ እና የቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በመምህራን እይታ…………………………..24
3.2.2. የተማሪዎች የንባብ ልምድ በመምህራን እይታ………………………………………27
3.2.3. የንባብ ልምድን በማሳደግ ረገድ ያለ ድርሻን አስመልክቶ መምህራን የሰጡት ምላ…..28

## ምእራፍ አራት

4. ማጠቃለያና የመፍትሄ
ሀሳቦች…………………………………………………………………………………..30
4.1. ማጠቃለያ…………………………………………………………………………..30
4.2. የመፍትሄ ሀሳቦች……………………………………………………………………31
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው
ዋቢ መጻህፍት
አባሪ

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎችን ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ መመዘን ነው። ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ት/ቢሮ የጉለሌ ክ/ከ ት/መምሪያ ስር በሚገኘው የየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት ነው። መረጃዎችም ከመምህራን እና ከተማሪዎች በመጠይቅ አማካኝነት ተሰብስበዋል።

ት/ቤቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተማሪ የሚያስተናግድ ሲሆን ሁሉንም ተማሪዎች መመዘን ስለማይቻል ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 80 ተማሪዎች በመጠይቁ ውስጥ ተካተዋል። የእነዚህን ተማሪዎች ምላሽ ለማረጋገጥም በት/ቤቱ የሚያስተምሩ 6 የቋንቋ መምህራን በመጠይቅ መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል። የተገኘው ውጤትም ተተንትኗል።

በጥናቱ የተገኘው ውጤትም የሚያመለክተው የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች የማንበብ ልምድ ዝቅተኛ እንደሆነ ነው። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው ተማሪዎች ስለ ንባብ ያላቸው ግንዛቤ እጅግ ዝቅተኛ መሆን፣ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ጫና፣ የትምህርት ቤቶች ንባብን በማስለመድ ረገድ ሊኖራቸው የሚገባ አስተዋጽኦ በሚገባ መወጣት አለመቻል ናቸው።

ስለዚህም ወደፊት ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ ለማዳበር ሊደረጉ ይገባቸዋል ብሎ አጥኚው የተወሰኑ ሀሳቦችን ሰንዝሯል። እነሱም የንባብ ክፍል ማዘጋጀት፣ ከፍተኛ ቅስቀሳ ማካሄድ እና ሳቢነት ያላቸውን ጽሁፎች በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ማካተት ናቸው።

# ምእራፍ አንድ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ማንበብ ከአራቱ የቋንቋ ክህሎቶች መካከል አንዱ እና እጅግ አስፈላጊው ክሂል ነው፡፡ አንድ ሠው ንባብ የሚጀምረው ፊደል መቁጠር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የተጀመረው የንባብ ልምድም ከግለሠቡ አካላዊ እድገት ጋር አብሮ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ በመጨረሻም ጤናማ እና ብሩህ የሆነ አዕምሮ ያለው ሠው እንዲፈጠር ይረዳል፡፡ የማንበብ ልምድ በዋነኝነት የሚዳብረው በትምህርት ቤት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚካሄደው ንባብ በአመዛኙ ከትምህርት ነክ ጽሑፎች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ከትምህርታቸው ውጭ የሆኑ ፅሁፎችን እንዲያነቡ ስለማይገደዱ የሚኖራቸው የንባብ ልምድ እጅግ ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ይህም ተማሪዎች ሊኖራቸው የሚገባውን ጠቅላላ ዕውቀት አነስተኛ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱንም አዝጋሚ ያደርገዋል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ከልጅነት ጀምሮ ከሚሰጥባቸው አላማዎች መካከል አንዱ የተማሪዎች የንባብ ክህሎት እና ልማድን ለማዳበር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቋንቋ ትምህርቱ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚማሯቸው የትምህርት አይነቶች ብቻ ሳይሆን ከትምህርታቸው ውጭ የሆኑ ነገሮችን የማንበብ ልምድን እንዲይዙ የማድረግ አላማም አለው፡፡ ከዚህ በተለየ አንዳንዶች በሀገራችን ያለው የንባብ ባህል በተለይም የተማሪዎች ከትምህርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸውን ጽሁፎች የማንበብ ልምድ እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ፤ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎችም ሊኖራቸው የሚገባውን ያህል የንባብ ልምድ እንዳላዳበሩ ሲናገሩ ይሰማል (ብርቱካን፣ 1993÷26)፡፡

እስከ አሁን የተማሪዎችን የንባብ ልምድ ከጽህፈት ክሂል፣ አንብቦ ከመረዳት፣ ከስነ-ልቦና ወዘተ … አንጻር የዳሰሱ በርከት ያሉ ጥናቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተካሂዷል፡፡ ይሁንና እስካሁን በተማሪዎች ከትምህርት ውጭ የሆኑ ፅሁፎችን የማንበብ ልምድ አስመልክቶ በቂ ጥናት አልተደረገም፡፡ ይህ ጥናት በእርግጥ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለመግባት እየተዘጋጁ ያሉ ተማሪዎች ከትምህርታቸው ውጭ

የሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ እንደሚባለው ዝቅተኛ መሆን አለመሆኑን በየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት ላይ በሚያደርገው ጥናት ለማረጋገጥ ይሞክራል።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ በየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ ምን ያህል እንደሆነ መመርመር ነው። በዚህ ዓብይ ዓላማ ስርም ጥናቱ ከዚህ የሚከተሉትን ንዑስ አላማዎች ይኖሩታል። እነሱም፡-

1) የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ ዝቅተኛ መሆን አለመሆኑን መመርመር፣
2) ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን በተመለከተ ያላቸው አተያይ ምን እንደሚመስል መፈተሽ፣
3) ተማሪዎች ትምህርት-ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማያነቡ ከሆነ ያለማንበባቸው ምክንያት ምን እንደሆነ ማጣራት፣ እንዲሁም
4) ተማሪዎች ከትምህርታቸው ውጭ የሆነ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ እንዲኖራቸው ምን መደረግ እንዳለበት የመፍትሄ ሃሳብ መጠቆም የሚሉት ናቸው።

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚካሄደው በየካቲት 12 የመሠናዶ ት/ቤት ሲሆን በቀጣይ ጊዜያት ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚገቡትን ተማሪዎች የንባብ ልማድ አስመልክቶ በሚሰጠው መረጃ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

1) የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ፅሁፎች የንባብ ልምድ ምን እንደሚመስል ወቅታዊ መረጃ ይሠጣል።
2) ተማሪዎች ስለ ንባብ ያላቸው አመለካከት ምን አይነት እንደሆነ መረጃ ይሠጣል
3) ዝቅተኛ የሆነ ትምህርት ነክ ያልሆኑ ፅሁፎችን የማንበብ ልምዳቸው ያላቸው ተማሪዎች ለምን ዝቅተኛ የንባብ ልምድ ሊኖራቸው እንደቻለ መረጃ ይሠጣል።
4) ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተያያዘ ቀጣይ ምርምር ለሚያካሂዱ አጥኚዎች መነሻ ሆኖ ያገለግላል

## 1.4. የጥናቱ ክልል

ይህ ጥናት ያተኮረው በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ት/ቢሮ ጉለሌ ክ/ከ ትምህርት መምሪያ ስር በሚገኘው የየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት ላይ ነው፡፡ ይህ ት/ቤት የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያትም ት/ቤቱ ለአጥኚው ካለው ቅርበት የተነሳ ነው፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድን አስመልክቶ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ጠቅላላው የንባብ ልምድን ማጥናት እጅግ ሠፊ ስለሚሆን ነው፡፡ ከክፍል ደረጃ አንጻርም ጥናቱ ከላይ በተጠቀሰው ትምህርት ቤት በ2001 ዓ.ም የ11ኛ ክፍል የመሰናዶ ተማሪዎችን ላይ ብቻ ያተኮረ ይሆናል፡፡

በየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት በአጠቃላይ 32 የአስራ አንደኛ ንዑስ ክፍሎች እንዲሁም 14 የአስራ ሁለተኛ ንዑስ ክፍሎች አሉ፡፡ ት/ቤቱ ካለው የተማሪ ቁጥር አንጻርም ሁሉንም ተማሪዎች በጥናቱ ማካተት ስለማይቻል አጥኚው የተወሰኑ ተማሪዎችን በመረጃ ሰጪ ናሙናነት መርጧል፡፡ ናሙና አወሳሰዱ በዋነኝነት ትኩረት ያረገው በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሆነበት አንዱ ምክንያት አንደኛ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለሀገር አቀፍ የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተና በዝግጅት ላይ በመሆናቸው ለጥናቱ አመቺ ስላልሆኑ ሁለተኛ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የ11ኛ ክፍልን ትምህርት በጥሩ ውጤት አልፈው የመጡ በመሆናቸው ዝቅተኛ ውጤት አምጥተው የወደቁ ተማሪዎችን ውጤት ሊያካትት ስለማይችል ነው፡፡

## 1.5. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ ይኸውም ጥናቱ ከተማሪዎችና ከመምህራን በመጠይቅ አማካኝነት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተንና በመተርጎም የማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ በማቅረብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉት መረጃዎችም በመረጃ ሰጪ ናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎችንና መምህራን መጠይቅ በማስሞላት የሚሰበሰብ ሲሆን የናሙና አመራረጥ ዘዴውም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡፡

በ11ኛ ክፍል ካሉት 32 ንዑስ ክፍሎች የነሲብ ናሙና አመራረጥ አካል የሆነውን የዕጣ ናሙና ስልት በመጠቀም 8 ንዑስ ክፍሎች (25 በመቶ) ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሁሉም ክፍሎች ስም በወረቀት ላይ ከተጻፈ በኋላ ተጠቅልሎ ዕጣ በማስወጣት የመጀመሪያዎች ስምንት ንዑስ ክፍሎች ተመርጠዋል፡፡ በተማሪዎች አመራረጥ በኩል በናሙና ከተወሰዱት ስምንት ንዑስ ክፍሎች ከእያንዳንዳቸው 10 ተማሪዎች መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርõል፡፡ ይህም በሁሉም ክፍሎች ያለው የተማሪ ቁጥር በአማካይ አርባ መሆኑን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ በተጨማሪም የጥናቱ ውጤት ወካይነት እንዲኖረው ከእያንዳንዱ ክፍል ከሚሞሉት 10 ተማሪዎች በኮታ ናሙና 5 ወንዶች እና 5 ሴቶች መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይሄውም በተማሪዎች ስም ዝርዝር መዝገብ ቁጥራቸው ከ1-20 ከሆኑ ተማሪዎች የመጀመሪያዎችን አምስት ወንዶች እና አምስት ሴቶች በመውሰድ ነው፡፡

የጥናቱ ውጤት የበለጠ አስተማማኝ እንዲሆን በትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ የማህበራዊ ሳይንስም ሆነ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች በጋራ ከሚወስዷቸው ትምህርቶች አንዱ በሆነው በቋንቋ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪዎች የንባብ ልምድን አስመልክቶ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የአማርኛና የእንግሊዝኛ መምህራኑ ብቻ ይህን መጠይቅ እንዲሞሉ የተደረገው፡- በሁለቱም የትምህርት ዘርፍ የሚማሩትን ተማሪዎች አስመልክቶ እውቀት ስላላቸውና የንባብ ልምድን አስመልክቶ ለሚደረግ ጥናት የቋንቋ መምህራኑ የተሻለ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለሚጠበቅ ነው፡፡

በመረጃ አተናተን በኩል ጥናቱ ሁለት ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በሰንጠረዥ ተካቶ በመቶኛ እየተሰላ የሚቀርብ ሲሆን ከእያንዳንዱ ሰንጠረዥ በኋላ ትንታኔ ቀርቧል፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ መምህራን የሰጡት ምላሽ ቀደም ሲል ተማሪዎቹ ከሰጡት ምላሽ ጋር እየተያየ ትንተናና ትርጎማ ተካሂዷል፡፡

# ምእራፍ ሁለት

## 2.1. ንባብ ምንድን ነው?

ስለንባብ ምንነት የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ጊዜ የተለያየ ብያኔ የሰጡ ሲሆን የአብዛኞቹ ምሁራን ብያኔም ተመሳሳይነት አለው፡፡ ስለንባብ ምንነት ከተሰጡ ብያኔዎች መካከልም ተስፋዬ ሸዋዬ (1981፡26) "ማንበብ አንድን መጽሃፍ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው መወጣት ወይም አንድን የቀረበ ጽሁፍ ከዳር እስከዳር ማንበልበል አይደለም፡፡" ብሏል፡፡ ከዚህ ብያኔ እንደምንረዳው ንባብ ማለት በወረቀት ላይ የሰፈረን ነገር ከዳር እስከዳር መሸምደድ ሳይሆን በጸሀፊውና በአንባቢው መካከል የሚደረግ የሥሜት ውህደት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ትሮይካ (112፡1998) ንባብን በሌላ መልኩ ሲያብራሩት ደግሞ

> "ንባብ ቃላትን ከመመልከት የዘለለ ንቃት የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ የንባብ ሂደት ጽሁፍን፣ አይን እና አእምሮን በአንድ ላይ ያካተተ ትርጉም የመፍጠር ሂደት ነው፡፡ በንባብ ጊዜ አእምሮአችን አስቀድሞ በምናውቀው፣ አሁን እየተማርነው ባለነው እና ለእኛ አዲስ በሆነ ነገር መካከል ትስስር ይፈጥራል፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከእኚህ ጸሀፊ ሀሳብ የምንረዳው በንባብ ጊዜ ፀሀፊው አዲስ ነገር እያስተማረን ወይም የምናውቀውን ነገር በአዲስ መልክ እያስታወሰን እንደሆነና፣ አእምሮአችን ደግሞ የምናነበውን እና በውስጣችን ያለውን እውቀት እያጣመረ እንደሚያደራጅ ነው፡፡ የሁለቱም ምሁራን ሀሳብ በድምሩ ሲታይም ንባብ የብዙ ክህሎቶች ውህደት እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡

## 2.2. የንባብ ጠቀሜታ

ንባብ የሰው ልጅ በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ እድገቱን የሚያፈጥንበት፣ ሰብእናውን የሚቀርጽበት እና ማንነቱ ጠፍቶ እንዳይቀር ጠብቆ የሚያቆይበት ሂደት ነው፡፡ ማንበብ የማይችል ግለሰብ ነገሮችን የማወቅና የመግለጽ ብቃቱ በማየት እና በመስማት ላይ ብቻ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት የግለሰቡ የአመለካከት ብቃት አነስተኛ እና የተዛባ ይሆናል፡፡ ቴይለይ (1973፡180) በዚህ ላይ አጽንኦት

ሰጥተው ሲናገሩ "ማንበብ የማይችል ህጻን በአመዛኙ መጻፍም የማይችል ህጻን ይሆናል፡፡ ስለዚህም ማንኛውም የፈጠራም ሆነ የእውነታ ጽሁፍ ዕውቀቶች ከማያነብ ሰው የተሰወሩ ናቸው፡፡" ከዚህ ገለጻ የምንረዳው አለምን ለመረዳት ጽሁፍ እጅጉን ጠቃሚ መሳሪያ እንደሆነ እና የማያነብ ሰውም የሚያጣው ነገር ያለ መሆኑን ነው፡፡

በማህበረሰብ ደረጃም ካየነው የማንበብ ልምድ የሌለው ማህበረሰብ ከእሱ በፊት ስለነበሩት ቀደምት ማንነቶቹ በተሟላ ሁኔታ የማያውቅ በመሆኑ "እኛ ማንነን?" የሚለው ጥያቄ ሁል ጊዜ እንዳስጨቀው ይኖራል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ የጽሁፍ ጥበብ እንዲዳብር የንባብ ልምድ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ "የጽሁፍ ጥበብ ማደግ ብቻውን ጥሩ ጸሃፊዎችን ባይፈጥርም እንኳን ንባብ ከፍተኛ የሆነ የቅድመ ሁኔታነት ድርሻን ይወጣል" በአንድ ማበረሰብ ውስጥ ጸሀፊዎች እንዲፈጠሩ አስቀድሞ የአንባቢዎችን መኖር ግድ ነው፡፡(ባይርኒ 1991፡9)፡፡

## 2.3. የንባብ አይነቶች

የተለያዩ የንባብ አይነቶች ያሉ ሲሆን ብርቱካን (1993፡9) ሀሪስን ጠቅሳ በሶስት እንደሚከፈሉ ገልጻለች፡፡ እነሱም ተግባራዊ ንባብ፣ የማሻሻል ንባብ እና የመዝናኛ ንባብ ናቸው፡፡

### 2.3.1. ተግባራዊ ንባብ/Functional reading/

ብዙ ጊዜ በትምህርት ሂደት ውስጥ የሚዘወተር የንባብ አይነት ነው፡፡ ይህ የንባብ አይነት ብዙውን ጊዜ በእቅድ እና በአላማ የሚከናወን ነው፡፡ አንድ ሰው አንድን ስራ ሲያከናውን ስራውን ለማከናወን ሲል የሚጠቀመው የንባብ ስልት ነው፡፡ ተማሪ በትምህርት ሂደት ውስጥ የሚያነባቸው መማሪያ መጻህፍት፣ ተመራማሪው በምርምር ሂደት ውስጥ የሚያነባቸው ዋቢ መጻህፍት /Reference/፣ የአንድን እቃ አጠቃቀም ለመረዳት እና በአገልግሎት ላይ ለማዋል የሚረዱ ጽሁፎች /Manuals/ ወዘተ… በዚህ የንባብ አይነት ውስጥ ይዳሰሳሉ፡፡

### 2.3.2. **የማሻሻል ንባብ** /developmental reading/

ይህ የንባብ አይነት ዋነኛ አላማው ተማሪዎች የንባብ ልምድ እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፤ መማር ለማንበብ የሚል ዋና ግብ አለው፡፡ በዚህ የንባብ አይነት የአንባቢው ዋና አላማ አንድን ግብ ለማሳካት ብሎ ማንበብ ወይም ንባብን እንደመዝናኛ መጠቀም ሳይሆን እራሱን ንባብን ለማሻሻል የሚያከናውነው ነው፡፡

### 2.3.3. **የመዝናኛ ንባብ** /recreational reading/

በዚህ የንባብ አይነት አንባቢው ንባብን የሚጠቀመው፣ ለመዝናኛ፣ ለማድነቅ፣ ለጊዜ ማሳለፊያ ወዘተ … አላማዎች ነው፡፡ ይሁን እንጂ ንባብን ለመዝናኛነት መጠቀም ንባቡን ፍሬ ቢስ አያደርገውም፡፡ ይልቁንም በመዝናናት ውስጥ የንባብ ልምድ ይዳብራል፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ይሻሻላል፤ የአስተሳሰብ አድማስ ይሰፋል፡፡ በተጨማሪ ይህ የንባብ አይነት እንደሌሎቹ የቦታና የጊዜ ሁኔታ አይጫነውም፡፡

## 2.4. የንባብ ደረጃዎች

በንባብ ሂደት አንባቢውን ሙሉ ትርጉም የማግኘት ደረጃ ላይ ያደርሳሉ የሚባሉ በተለያዩ ምሁራን የተጠቀሱ የንባብ ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህን ደረጃዎች ናታል (1981፡82) በአራት ሲከፍሉአቸው በድሉ (1996፡25) ደግሞ በሶስት ከፍሎአቸዋል፡፡ የናታል አከፋፈል ከትርጉም መፍጠር አንጻር ሲሆን የበድሉ ደግሞ ከጊዜ አንጻር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱንም ሀሳብ በአንድ ላይ አካቶ የያዘውን የትሮይካ (1998፡118) አከፋፈልን እንወስዳለን፡፡ በዚህ አከፋፈል ንባብ ሶስት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እነሱም እማሬያዊ ንባብ፣ ፍካሬያዊ ንባብ እና የምዘና ንባብ ናቸው፡፡

### 2.4.1. **እማሬያዊ ንባብ** /reading for **Literal meaning/**

ይህ የመጀመሪያው የንባብ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ የንባብ ደረጃ የተባለውን ከመረዳት በዘለለ ስለ ፅሁፉ የአንባቢውን አስተያየት ወይም ስሜት መረዳት አያጠቃልልም፡፡ ብዙውን ጊዜ ለመረጃ ለመስጠት አላማ ተብለው የሚጻፉ ጽሁፎች በዚህ የንባብ ደረጃ እንዲነበቡ ተደርገው ይዘጋጃሉ፡፡ በእማሬያዊ ንባብ የሚታዩ ነገሮች አንደኛ መልእክት ሲሆን ሁለተኛ ለንባቡ ቅርጽ የሰጡት ትናንሽ ነገሮች ናቸው፡፡

#### 2.4.2. **ፍካሬያዊ ንባብ** /reading to make inference/

በዚህ የንባብ ደረጃ አንባቢው የተጻፈውን ሳይሆን ጻሀፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት ደረጃ ነው፡፡ መረጃ ማጣቀስ፤ዳራ መፈለግ እንዲሁም የጸሀፊውን አላማ ለማግኘት መጣር በዚህ የንባብ ደረጃ የሚከወኑ ተግባሮች ናቸው፡፡

#### 2.4.3. **የምዘና ንባብ** / reading to Evaluate/

የምዘና ንባብ ብዙ ችሎታዎችን አጣምሮ መጠቀምን የሚጠይቅ የንባብ ደረጃ ነው፡፡ የጸሀፊው ድምጸት ያመጣውን ተጽእኖ መረዳት፣ ወገንተኝነት ካለ ማየት እንዲሁም ዕውነታ (fact) እና አስተያየትን ለይቶ ማስቀመጥ የመሳሰሉ ጉዳዮች በዚህ ደረጃ ይታያሉ፡፡ አንባቢዎች አሉታዊ ይዘት ኖሯቸው በአዎንታዊ መልክ የሚቀርቡ ጽሁፎችን መረዳት፣ መረጃዎችን እና አስተያየቶችን ቀላቅለው የሚያቀርቡ ጽሁፎች በሚገባ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.5 የአነባበብ ቴክኒኮች(ስልቶች)

አንድ አንባቢ ለማንበብ ሲነሳ እንደሚይዘው አላማ አይነት የተለያዩ የንባብ ቴክኒኮች ሊጠቀም ይችላል፡፡ አያሌው (1996፡6) አራት አይነት የአነባበብ ስልቶች እንዳሉ ገልጿል፡፡

#### 2.5.1 **የአሰሳ ንባብ** /scanning/

የአሰሳ ንባብ የተወሰኑ ዋና ሀሳቦችን ለማግኘት የሚደረግ ፈጣን የአነባበብ ስልት ነው፡፡ ናታል (1982፡19) ይህ የንባብ ስልት ምንም አይነት ቅደም ተከተል ሳይጠብቅ ከአንድ ጽሁፍ ተፈላጊውን የተወሰነ መረጃ ለመለየት የምንጠቀምበት ስልት ነው በማለት ይገልፃሉ ፡፡ይኸውም አንባቢው ተፈላጊውን መረጃ ካገኘ ጽሁፉን እስከ መጨረሻ ለማንበብ አይገደድም፡፡ በዚህ የአነባበብ ስልት ከሚነበቡ ነገሮች መካከል የሠው ስም፣ የቦታ ስያሜ፣ ዓመተ ምህረት፣ ቀናት፣ የስልክ ቁጥር ማውጫ፣ የምግብ ዝርዝር ወዘተ… ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

#### 2.5.2 ግርፍ ንባብ /Skimming

ይህ ደግሞ የጽሁፍን ዋና ጭብጥ ለይቶ ለማወቅ ሲባል በፍጥነት የሚካሄድ ንባብ ነው፡፡ ናታል (1982፡19) ይህን ሲያስረዱ "በግርፍ ንባብ ጊዜ ፅሁፉ እንዴት እንደተዋቀረ፣ በውስጡ ያለውን ድምጸት እና የጸሀፊውን ፍላጎት በፍጥነት እንዳስሳለን" ብለዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ያነባበብ ስልት ቃል በቃል ማንበብ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በዚህ ፈንታ ዋናውን ርዕስ፣ ንዑስ ርእሶችን ወይም የእያዳንዱን አንቀፅ ሀሳብ በመረዳት በአጠቃላይ የጽሁፉን ይዘት ማወቅ ይቻላል፡፡

#### 2.5.3 ሰፊ ንባብ /Extensive reading

ይህ እንደ ግርፍ ንባብ ወይም እንደ አሰሳ ንባብ በጥድፊያ የሚካሄድ ሳይሆን ጊዜ ተወስዶበት በተረጋጋ መንፈስ የሚካሄድ ንባብ ነው፡፡ ግሪሌት (1981፡4) የመጠነ ሰፊ ንባብን አገልግሎት ሲያስረዱ "ለግል ደስታ፣ ለመዝናናትና አጠቃላይ የሆነ እውቀት ለመጨበጥ የሚያስችል ንባብ ነው" ብለዋል፡፡ የጽሁፉ አይነትም ረዘም እና ሰፋ ያለ ነው፡፡ በዚህ የአነባበብ ቴክኒክ ከሚካተቱ ጽሁፎች መካከል ልቦለዶች እና ጋዜጦች ለምሳሌነት ይቀርባሉ፡፡

#### 2.5.4 ጥቅል ንባብ /Intensive reading

ይህ ንባብ የተወሰነ መረጃና እውቀት ለማግኘት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ዝርዝር ነገሮች የሚታዩበት የአነባበብ መንገድ ነው (ብሩክስ 1964፡172)፡፡አላማው በጣም ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መርምሮ ማውጣት በመሆኑ ከምንም በላይ የአንባቢውን ንቁነት እና ትኩረት ይፈልጋል፡፡ በተጨማሪም አንባቢው በጽሁፍ የተገለጸው መረጃ የቀረበበትን መንገድ የሚመረምርበት ስልት በመሆኑ በንባቡ ሂደት ውስጥ እርጋታ እና ጥንቃቄ የግድ ነው፡፡ ተፈላጊው መረጃ እስኪገኝም ጽሁፉን ቃል በቃል፣ ሀረግ በሀረግ፣ ዐረፍተ ነገር በአረፍተ ነገር እናነበዋለን፡፡

### 2.6 የንባብ ልማድ እንዲዳብር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ አካላት

የንባብ ባህል የፅሁፍ ልማድ ባላቸው ቋንቋ ጠጠቃሚዎች ሁሉ የተለመደ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንዲዳብር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ብለው ኤበርሶልድ እና ሜሪ (1997፡7-

8) የጠቀሷቸው አምስት አካላትን ነው፡፡ እነሱም ቤተሰብ፣ ማሕበረሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ ባህል እና ግላዊ ባህሪ ናቸው፡፡

### 2.6.1 ቤተሰብ

የንባብ ልምድ ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች በአካባያቸው ያሉ አንባቢያንን በመከተል የንባብ ባህልን ያዳብራሉ፡፡ ኤበርሶልድ እና ሜሪ (1997፡7) ይህን ነገር በቤተሰብ ደረጃ እንዴት እንደሆነ ሲገልጹ "በጋዜጦች፣ በመጽሄቶች እና በመጽሀፍት የተሞሉ ቤቶች ለህጻናት የንባብን ጠቀሜታ በተመለከተ ግልጽ መልእክት ያስተላልፋሉ"ይላሉ ይህ ገለጻ እንደሚያሳየው የሚነበቡ ነገሮች በበዙበት ቤት ውስጥ ያሉ ወጣቶች የንባብ ባህልን ይወርሳሉ፡፡ መረጃ ለማግኘት፣ ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ሁኔታዎችን ለመከታተል፣ አዳዲስ ነገሮችን ለመማር ወይም ለመዝናናት ከሌሎች ዘዴዎች ይልቅ ንባብን ምርጫቸውም ያደርጋሉ፡፡

### 2.6.2 ማህበረሰብ

አንድ አይነት የአኗኗር ዘይቤ፣ የስነ-ምግባር መርሆዎች፣ የዕውቀት መለኪያዎች እና ርዕዮተ ዓለም ያለው የሠዎች ስብስብ ማህበረሰብ ይባላል፡፡ ንባብ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ቦታ፣ ለሚያነቡ ሠዎች ማህበረሰቡ የሚሰጠው ደረጃ፣ ንባብን እንደ አስፈላጊ የህይወት ተግባር ወይም እንደ ትርፍ ስራ የሚመለከትበት ሂደት የንባብ ልማድ በሚኖረው እድገት ላይ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ንባብን እንደ አንድ መገለጫ ባህል አድርጎ በሚወስድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ወጣቶች የተሻለ የንባብ ልምድን ሲያዳብሩ ንባብን በቀዳሚ ምርጫነት ባልያዘ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ወጣቶች የሕይወታቸው አንድ አካል አርገው ይይዙታል ማለት ያስቸግራል፡፡

### 2.6.3 ትምህርት ቤት

ከቤተሰብ እና ከማህበረሰብ በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች የንባብ ባህል እንዲዳብር በማስቻል ረገድ እጅግ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ምክንያቱም ትምህርትን ከንባብ ለይቶ ማየት ስለማይቻል ነው፡፡ ተማሪዎች እንዲያነቡ የሚያበረታቱ መምህራን እና ጥሩ ቤተ መጻህፍት ባለበት ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ ወጣቶች የተሻለ የንባብ ልምድ ይኖራቸዋል፡፡ ናታል (1981፡171) ይህን ሲገልጸው "የንባብ ባህል

በሚበረታታበት እና የሚነበቡ መጻህፍት ባሉባቸው ት/ቤቶች በሳምንት አንድ እና ከዚያ በላይ መፃህፍትን የሚያነቡ ተማሪዎችን ማግኘት አዲስ አይደለም፡፡

### 2.6.4 ባህል

"ባህል ሰዎች በዙሪያቸው ያለውን ማህበራዊ እውነታ የሚረዱበት፣ የሚተረጉሙበት፣ የሚገልጹበት እና ምላሽ የሚሰጡበት የጋራ የሆነ እውቀት እና ስርአት ነው፡፡" ሊድራች (1995፡5) የሰው ልጅ ማህበራዊ እውነታን ከሚረዳባቸው የባህል ዘርፎቸ አንዱ የንባብ ባህል ነው፡፡ ባህል የንባብን ልማድ በመቅረጽ ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ኤበርሶልድ እና ሜሪ (1997፡8) ሲያስረዱ "የተለያዩ በባህል ውስጥ የሚገኙ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቡድኖች የተለያዩ የንባብ ጠቀሜታዎችን ቢያስቀምጡም ትልልቆቹ የባህል እሴቶች ማህበረሰቡ የሚይዘውን የንባብ አመለካከት ይቀርጻሉ፡፡" ከምሁራኑ ገለጻ እንደምንረዳው ሠዎች ባህላቸው ከቀረጸላቸው ውጭ ማሰብም ሆነ ማድረግ አይፈልጉም፡፡ የንባብን ዋጋ ከፍ የሚያደርግ ባህልም ልማዱ እንዲዳብር ያደርገዋል፡፡

### 2.6.5. ግላዊ ባህሪ

ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ት/ቤቶች እና ባህል በአንድ ሰው የንባብ ልማድ ላይ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ እና የሚፈጥሩበትን ተጽእኖ የሚያስተናግድበት መንገድ የንባብ ልምዱን ይወስኑታል፡፡ በተጨማሪም በቋንቋ ትምህርት ወቅት ተጽእኖ ፈጣሪ የሚባሉት ግላዊ ባህሪዎች ማለትም ተነሳሽነት፣ ትኩረት፣ ሃላፊነት መውሰድ፣ ለራስ ያለ አዎእታዊ አመለካከት እና እርጋታ የንባብ ልምድን በማዳበር ላይ ይሰራሉ፡፡ ኤበርሶልድ እና ሜሪ (1997፡8)

## 2.7. ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች

ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች የሚባሉት አዲስ ዕውቀትን ወይም መረጃን ለማግኘት ሳይሆን ለመዝናናት፣ ጊዜ ለማሳለፍና፣ ለማድነቅ ወዘተ... ተብለው የሚነበቡ የጽሁፍ አይነቶች ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከትምህርታቸው ውጭ፣ ሠራተኞች ከስራቸው ውጭ እንዲሁም ተመራማሪዎች ከምርምራቸው ጋር ባልተያያዘ የሚያነቧቸውን ጽሁፎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ፅሁፎች እንላቸዋለን፡፡ በድሉ (1996፡28) ትምህርት

ነክ ያልሆኑ ፅሁፎች ያላቸውን አስፈላጊነት ከተማሪዎች ጋር አያይዞ ሲያስረዳ “የተማሪዎች የንባብ ችሎታ ግብ መማሪያ ክፍል ብቻ መሆን የለበትም። ይልቁንም ከትምህርት ቤት ባሻገር ያለ ህይወታቸውን ግብ ያደረገ መሆን አለበት” ብሏል። በትምህርት ነክ ጽሁፎች ውስጥ ከሚካተቱ ነገሮች መካከል ልቦለዶች፣ ጋዜጦች፣ መጽሄቶች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ የሃይማኖትና የታሪክ መጻኅፍት ወዘተ… ሊካተቱ ይችላሉ። ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች ከአገልግሎታቸው አንጻር በሰፊ የንባብ ስልት /Extensive reading/ ይዳሰሳሉ ግሪሌት (1981፡4)።

## 2.8. የንባብ ምርጫ

የንባብ ምርጫን አስመልክቶ ይህ ነው የሚል ብያኔ መስጠት ያስቸግራል። ምክንያቱም ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚያስፈልጉ እንደ እድሜ እና ዜግነት ወዘተ… የመሳሰሉ ነገሮች ስላሉ ነው። ናታል (1981፡25) የንባብ ምርጫ በሶስት ነገሮች እንደሚወሰን ገልጸዋል። እነሱም ተነባቢነት፣ የይዘት ተስማሚነት እና ትምህርት ሰጪነት ናቸው። ተነባቢነት /readability/ ብዙውን ጊዜ ከቋንቋ ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው። ይሁን እንጂ ናታል (1981፡25) ስለተነባቢነት ሲናገሩ ተነባቢነት የሰዋሰው መወሳሰብ ወይም የቃላት ክብደት ጉዳይ ብቻ አይደለም” ብለዋል። ከገለጻው እንደምንረዳው ተነባቢነት ከዚህም በዘለለ የዘይቤ አጠቃቀም፣ የአፃፃፍ ስልት እና የፅሁፍ አላማ ጉዳይ ነው። ሌላው የንባብ ምርጫን የሚወስነው ጉዳይ የይዘት ተስማሚነት (Suitability of content) ነው። አንባቢዎች የሚያነቡትን ነገር ይዘቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አይጠቅመንም ብለው ካሰቡ የንባብ ምርጫቸውን ይቀይራሉ። ሌላው በንባብ ምርጫ ላይ እጅግ ወሳኝ እና ጠቃሚ የሆነው ነገር ትምህርት ሰጪነት /Exploitability/ ነው። ናታል (1981፡25) ይህን ወሳኝነት ሲያስረዱ “ከሌሎቹ በበለጠ ከፍላጎት ቀጥሎ ትምህርት ሰጪነት እጅግ አስፈላጊ ነው” ብለዋል። ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው አንድ ሰው የሚያነበውን ነገር ምንም ያህል ቢወደው እንኳ ትምህርት ሰጪነት ከሌለው ጥቅምም ሆነ ተመራጭነት እንደሌለው ነው።

## 2.9. ጠቃሚ የአነባበብ ቴክኒኮች

ጠቃሚ የሚባሉ የአነባበብ ቴክኒኮችን ግሪሴት በሶስት ከፍለዋቸዋል፡፡ እነሱም በፍጥነት ማንበብ እና የአሰሳ ንባብን መልመድ ናቸው (ግሪሴት 1981፡14)፡፡

### 2.9.1. ስሜትን መረዳት /Sensitizing/

በዚህ ውስጥ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ያሉ ሲሆን አንባቢው የማያውቃቸው ቃላት ወይም የተወሳሰቡ ዓ.ነገሮች ሲያጋጥሙት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ስልቶች በመጠቀም ችግሩን መፍታት ይችላል፡፡ ይኸውም ኢንፈር (Infer) በማድረግ በዓ.ነገሮች መካከል ያለ ግንኙነት በመረዳት እንዲሁም ዓ.ነገሮችእና ሀሳቦችን በማገናዘብ በሚያገኘው ትርጉም ፣ የማያውቃቸውን ቃላት እና የተወሳሰቡ ዓ.ነገሮች ትርጉም መረዳት ይቻላል፡፡ (ግሪሴት 1981፡15)

### 2.9.2. የንባብ ፍጥነትን ማሻሻል

"ቀርፋፋ አንባቢዎች በቀላሉ ንባባቸውን ሊያsርጡ ይችላሉ" (ግሪሴት 1981፡16) ከዚህ አገላለጽ የምንረዳው ንባብ እና ፍጥነት ያላቸውን ጥብቅ ግንኙነት ነው፡፡ በፍጥነት የማንበብ ልማድን ማዳበር ብዙ ፅሁፎችን በአጭር ጊዜ በማንበብ ብዙ ዕውቀትን እንዲያገኝ እና የንባብ ጥቅም እንዲረዳ ያደርገዋል፡፡

### 2.9.3. የአሰሳ ንባብ /Scanning/ መለማመድ

የአሰሳ ንባብ የተወሰኑ ዋና ሃሳቦችን ለማግኘት የሚደረግ ፈጣን የአነባበብ ስልት ነው፡፡ ናታል (1992፡19) የዚህ የንባብ ዘዴ ዋና ጠቀሜታው ተፈላጊውን መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለይተን የምናወጣበት ስልት መሆኑ ነው ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ በተለይም ተማሪዎች ጥቂት መረጃ ለማግኘት ብዙ አላስፈላጊ ነገሮችን ሲያነቡ ይታያል፡፡ ግሪሴት (1981፡17) ይህን ሲያስረዱ "ተማሪዎች ሁሉንም ጽሁፎች በአንድ መንገድ በማንበብ ጊዜ ሲያባክኑ እና ጠቀሜታ ያላቸው ሃሳቦች ሲዘነጉ እናያለን፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጥቅም የሌላቸው መረጃዎችን ሲለሚወስዱ ነው" ይላሉ፡፡ እንደ ምሁራኑ አገላለጽ ይህን ችግር ለመቅረፍ የሚመከሩት ነገሮች ቀጥሎ የሚመጣውን ነገር መገመት /Predicting/፤ ማውጫዎች፣ መቅድሞች ወዘተ… ላይ ቅድመ ምልከታ ማድረግ /Previewing/፤

ግንዛቤ መውሰድ፣ በመጨረሻም የአሰሳ ንባብ ላይ መድረስ ናቸው (ግሪሴት 1981፡17-19)፡፡

## 2.10. የተሳሳቱ የአነባበብ ቴክኒኮች

ናታል (1981፡37-38) በአብዛኛው የሚታዩ ያሏቸው የተሳሳቱ የአነባበብ ቴክኒኮች ሶስት ናቸው፡፡ እነሱም ድምጽ እያሰሙ ማንበብ፣ በጣት መጠቆም እና ወደኋላ መመለስ ናቸው፡፡

### 2.10.1. ድምጽ እያሰሙ ማንበብ /Subvocalizing/

ይህ የንባብ ቴክኒክ ህጻናት ለመጀመሪያ ጊዜ ንባብን በሚለማመዱበት ጊዜ የሚያደርጉት ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ አንባቢዎች እያደጉ በሚሄዱበት ወቅትም ይህን ቴክኒክ ይዘውት ይሄዳሉ፡፡ ይህ አይነት አነባበብ ንባቡን ዝግ የሚያደርግ፣ ጠቅላላ ይዘቱን የመረዳት ሳይሆን ቃል በቃል የመቁጠር ሂደት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በሌሎች ላይ የመረበሽን ስሜት ይፈጥራል፡፡

### 2.10.2. በጣት መጠቆም /Finger pointing/

ይህ የንባብ ቴክኒክም በተመሳሳይ መልኩ ህጻናት በሚያነቡበት ፊደል ላይ ትኩረት ለማድረግ የሚጠቀሙበት ስልት ነው፡፡ ነገር ግን ንባቡን ቀርፋፋ እና ቃላትን የመቁጠር ስራ ያደርገዋል፡፡ በተለይም አንባቢው የሚያነበውን ነገር በእጁ ካልያዘ ወይም በርቀት የተቀመጠ ከሆነ ንባቡን ለማከናወን ይቸገራል፡፡

### 2.10.3. ወደኋላ መመለስ /Regression/

አንዳንድ አንባቢዎች ያነበቡትን ነገር ወደኋላ እየተመለሱ ደግመው ያነቡታል፡፡ ይህም ንባቡን ዝግ ያለ፣ አድካሚ እና ጊዜ የሚፈጅ ያደርገዋል፡፡ በእርግጥ አንዳንዶች ንቁ እና ምላሽ የሚሰጡ /Active and Responsive/ አንባቢዎች ሚያነቡትን ነገር ለመረዳት የሚጠቀሙበት ስልት ስለሆነ እንደ ስህተት ሊታይ አይገባውም የሚሉ ወገኖች ቢኖሩም ሌሎች ደግሞ አንድን ነገር ደጋግሞ ማንበብ ትኩረት የማጣት ምልክት ነው የሚሉም አሉ፡፡

# ምእራፍ ሶስት

## 3. የጥናቱ ውጤት ትንተና

በምእራፍ አንድ ላይ እንደገለጠው ይህ ጥናት የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ት/ቢሮ ጉለሌ ክ/ከ/ት/መምሪያ ስር በሚገኘው የካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የተማሪዎችን ትምህርት ነክ ያልሆኑት ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ በመመዘን ላይ ያተኩራል፡፡ ለዚህም ከተማሪዎች እና ከመምህራን በተለያዩ መጠይቆች አማካኝነት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተገኘውን ምላሽም እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

### 3.1. የተማሪዎች ምላሽ ትንተና

ከተማሪዎች የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች

| | ፆታ | | እድሜ | | | ትምህርት ዘርፍ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አማራጮች | ወ | ሴ | ከ16-20 | ከ20-25 | ከ25በላይ | ተፈጥሮ ሳይንስ | ማበራዊ ሳይንስ |
| ድምር | 38 | 38 | 71 | 3 | 2 | 50 | 26 |
| በመቶኛ | 47.5 | 47.5 | 93.01 | 3.9 | 2.99 | 65.5 | 34.5 |

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው በጥናቱ ውስጥ መጠይቅ በመሙላት እንዲሳተፉ ከታቀዱት 80 ተማሪዎች መካከል 76 ወይም 95% የሚሆኑት መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል፡፡ መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት ሰባ ስድስት ተማሪዎች መካከል 93.01% ዕድሜያቸው ከ16-20 ባለው መካከል ሲሆን 3.9% ከ20-25 በሚገኘው ዕድሜ ውስጥ 2.99% ከ25 ዓመት በላይ ናቸው፡፡ ከትምህርት ዘርፍ አንጻር ስንመለከትም 65.5% የሚሆኑት የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ሲሆኑ 34.5% የሚሆኑት ደግሞ የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ተማሪዎች በመጠይቁ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሠጡት ምላሽ እንመለከታለን፡፡

### 3.1.1. ትምህርት ነክ ያልሆኑ ፅሁፎችን የማንበብ ልምድን አስመልክቶ ተማሪዎች የሠጡት ምላሽ ትንተና

ሠንጠረዥ 1፡- የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ደረጃ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከመደበኛ የመማሪያ መጻህፍት ውጭ ያሉ ፅሁፎችን የማንበብ ልምድህ/ሽ ምን ያህል ነው? | | | |
| | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | ዝቅተኛ | ምንም አላነብም |
| ብዛት | 6 | 32 | 33 | 5 |
| % | 7.86 | 41.92 | 43.23 | 6.55 |
| 8 | በግምት እስከአሁን ምን ያህል መጻህፍት አንብበሀል/ሻል? | | | |
| | ከ30 በላይ | ከ20-30 | ከ10-20 | ከ10 በታ |
| ብዛት | 8 | 10 | 20 | 33 |
| % | 11.2 | 14 | 28 | 46.2 |

ሠንጠረዡ እንደሚያሳየን 43.23% የሚሆኑት ተማሪዎች ከመደበኛ የመማሪያ መጻህፍት ውጭ የማንበብ ልምዳቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ሲገልፁ በቁጥር በጥቂት የሚያንሱ ተማሪዎች ማለትም 41.92% የሚሆኑት ከመደበኛ የመማሪያ መጻህፍት ውጭ ያሉ ፅሁፎችን በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያነቡ ገልጸዋል፡፡ 7.86% ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ የሆነ የማንበብ ልምድ ያላቸው ሲሆን 6.55% የሚሆኑት ተማሪዎች ከመደበኛ የመማሪያ መጻህፍት ውጭ ምንም አላነብም ብለዋል፡፡

ይሁን እንጂ ከፍተኛ የማንበብ ልምድ አለን በሚሉ እና የማንበብ ልምዳችን ዝቅተኛ ነው በሚሉ ተማሪዎች መካከል የቁጥር መመጣጠን ያለ በመሆኑ፣ ከፍተኛነት ወይም ዝቅተኛነት የአንጻራዊነት ጉዳይ በመሆኑ እንዲሁም ይህን ያህል ያነበበ በከፍተኛ ደረጃ አንባቢ ነው ይህን ያህል ያነበበ ደግሞ የንባብ ልምዱ ዝቅተኛ ነው ለማለት የሚያስችል መመዘኛ ባለመኖሩ ተማሪዎች በቁጥር 1 የሰጡትን መልስ በቁጥር 8 ላይ በሰጡት መልስ ለማመሳከር ተሞክሯል፡፡ በቁጥር 8 ላይ እስከ አሁን ያነበቡትን መጻህፍት ብዛት በግምት ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሰረት ምንም አላነብም የሚል መልስ ከሰጡት ተማሪዎች ውጭ ያሉት ተማሪዎች ለዚህ ጥያቄ የሠጡት መልስ ታይቷል፡፡ 11.2% ተማሪዎች ከ30 በላይ መጻህፍት አንብበናል ሲሉ 14% ከ20-30 መፅሀፍ አንብበናል ብለዋል፡፡ ከ10-20 መፅሀፍ ያነበቡት 28% ሲሆኑ ከ10 በታች መጻሀፍ ያነበቡ 46.2% የሚሆኑ ተማሪዎች ናቸው፡፡

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው በጣም ከፍተኛ የሚል መልስ በቁጥር 1 ላይ በሰጡት መካከል እና በቁጥር 8 ላይ ከ30 በላይ መጻህፍት አንብበናል በሚሉ መካከል መቀራረብ አለ፡፡ እንዲሁም ከ10 በታች መጽሀፍ ባነበቡ እና ከመማሪያ መጻህፍት ውጭ የማንበብ ልምዳቸው ዝቅተኛ በሆኑት መካከል መቀራረብ አለ፡፡ ይህ የሚያመለክተው ከፍተኛ የማንበብ ልምድ አለን በሚሉ እና ባነበቡት መጻህፍት ቁጥር መካከል የግንዛቤ ልዩነት እንዳለ ነው፡፡ የተወሰኑት ከሃያ እስከ ሰላሳ መጻህፍት ማንበባቸውን ከፍተኛ ሲሉት ሌሎች ደግሞ ከአስር እስከ ሃያ መጻህፍት ማበባቸውን ከፍተኛ ነው ይሉታል ብለን መደምደም እንችላለን፡፡

ከዚህ ውጤት መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ስለንባብ መጠን ያላቸው ግንዛቤ የተዘበራረቀ እንደሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም የሰጡት ምላሽ የንባብ ልምዳቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡ ግማሽ ያህሉ ተማሪዎች ምንም እንደማያነቡ ወይም ዝቅተኛ የሆነ የማንበብ ልምድ እንዳላቸው ሲያረጋግጡ 88.2% የሚሆኑ ተማሪዎች ያነበቡት መጻህፍት ብዛት ከ30 በታች ነው፡፡

ይሁን እንጂ የዚህ ጥናት አላማ የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድን መመዘን ብቻ ሳይሆን የሚያነቡት የንባብ ልምዳቸው ከየት እንደመነጨ ማወቅ የንባብ ልምዳቸው አነስተኛ የሆነ ወይም ምንም አይነት የንባብ ልምድ የሌላቸውን ምክንያታቸውን ማወቅ እና የመፍትሄ ሃሳብ መጠቆም ነው፡፡ የንባብ ልምዳችን ዝቅተኛ ነው ወይም ምንም አላነብም ብለው በጥያቄ ቁጥር 1 መልስ ለሰጡ ተማሪዎች በጥያቄ ቁጥር 2 ላይ ምክንያታቸውን ተጠይቀዋል፡፡

ሰንጠረዥ 2፡- የንባብ ድርሻ ትርፍ ጊዜን ከማሳለፍ አንጻር

| | ጥያቄ | አማራጮች | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| 2 | በተራ ቁጥር 1 ላይ ለቀረበው ጥያቄ መልስህ ሐ ወይም መ ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ትላለህ? | ሀ. ፍላጎት ስለሌለኝ<br>ለ. ጊዜ ስለሌለኝ<br>ሐ. የማንበቢያ ቦታ እጥረት<br>መ. የመጻህፍት እጥረት | 16<br>10<br>3<br>10 | 39.4<br>26.31<br>7.89<br>26.31 |
| 3 | ትርፍ ጊዜህን በምን ታሣልፋለህ/ታሳልፊያለሽ | - ፊልም በማየት<br>- ኳስ በመጫወት<br>- እምነት ነክ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ<br>- በማንበብ<br>- በመዝናናት<br>- በስራ | 37<br>4<br>3<br>20<br>4<br>3 | 51.8<br>5.6<br>4.2<br>28<br>5.6<br>4.2 |

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው ለተማሪዎች የንባብ ልምድ ማነስ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው የንባብ ፍላጎት ማጣት ነው፡፡ የጊዜ ማጣት እና የመጻህፍት እጥረት እኩል 26.31% የሆነ ተጽእኖ አላቸው፡፡ ይሁንና ተማሪዎቹ የቀን ተማሪዎች በመሆናቸው ዋና ስራቸው መማር ነው፡፡ የተወሰኑት ተማሪዎች በአንዳንድ ምክንያቶች የጊዜ እጥረት ሊያጋጥማቸው ቢችልም እንኳ 26.3% የሚሆኑት ተማሪ በጊዜ ማጣት ከንባብ ይርቃሉ ማለት አይቻልም፡፡

በተመሳሳይ በመጻህፍት እጥረት እና በማንበቢያ ቦታ እጥረት የሚል ምክንያት የሰጡትንም ስናይ የሚማሩበት ት/ቤት የሚገኝበትን ቦታ ስናስተውል እና ተማሪዎችም ከት/ቤቱ ብዙም ያልራቁ መሆናቸውን ስናስብ ይህንን ምላሽ እንጠራጠራለን፡፡ ተማሪዎች ለንባብ ፍላጎት እና ጊዜ ከሌላቸው ጊዜያቸውን በምን እያሳለፉ ነው የሚውሉት? በትርፍ ጊዜአቸውን ምንድን ነው የሚሰሩት? ብለን እንጠይቃለን፡፡ ለዚህም በተራ ቁጥር 3 ተማሪዎች ትርፍ ጊዜአቸውን በምን እንደሚያሳፉ የቀረበላቸውን ጥያቄ ውጤት መመልከት እንችላለን፡፡

በጥያቄ ቁጥር 3 ላይ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳየው ውጤት ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በተማሪዎች ህይወት ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ ድርሻ ነው፡፡ ማክጌሪ (2003፡28) የዚህን ጉዳይ አለም አቀፋዊነት ሲያስረዱ

> "በሰለጠኑ እና እንዱስትሪያላይዝድ በሚባሉት አገሮች እንኳን የሚረብሽ የትምህርት እና የንባብ ልምድ መውረድ ይታያል፡፡ በቅርቡ በስኮቲሽ የስነ-ጥበብ ካውንስል የተሰራ ጥናት እንዳሳየው የአስራ አምስት አመት እድሜ ካላቸው 15 ልጆች መካከል አንዱ ብቻ በሳምንት ውስጥ ከሶስት ሰአት በላይ የሚያነብ ሲሆን በአንጻሩ ቴሌቪዥን ከአስራ ዘጠኝ ሰአታት በላይ ይሸፍናል፡፡"

ይህ ፅሁፍ እንደሚያሳየው ቴሌቪዥን በአለም አቀፍ ደረጃ በሰዎች ህይወት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው ነገር መሆኑን ነው፡፡ በሰንጠረዡ ላይ እንደምናየው 51.8% የሚሆኑት ተማሪዎች ትርፍ ጊዜአቸውን ፊልም በማየት የሚያሳልፉ ናቸው፡፡ 28% የሚሆኑት ተማሪዎች ብቻ ንባብ በትርፍ ጊዜአቸው ተመራጭ ጊዜ ማሳለፊያቸው ሲሆን 4.2% በስራ ያሳልፋሉ፡፡ በማንበብ ትርፍ ጊዜአቸውን ከሚያሳልፉት 28% ተማሪዎች እና በስራ ከሚያሳልፉት ተማሪዎች ውጭ ያሉትን ተማሪዎች መልስ ስንመለከት ተማሪዎች ለንባብ ፍላጎትም ሆነ ጊዜ ያጡበትን ምክንያት ማወቅ እንችላለን፡፡ ይህም በዋነኝነት በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች መብዛት ነው፡፡ በተጨማሪም እንደ ኳስ መጫወት እና መንፈሳዊ ነገሮች ላይ ያለ ተሳትፎ ከንባብ በበለጠ ለተማሪዎች ትርፍ ጊዜ ማሳለፊያነት ተመራጭ ናቸው፡፡

### 3.1.2. የንባብ ምርጫን አስመልክቶ የተማሪዎች ምላሽ ትንተና

ሰንጠረዥ 3፦ የተማሪዎች የንባብ ምርጫን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4 | ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የምታነብ ከሆነ ምንድነው የምታነበው/ቢው? | | | |
| | ልቦለድ | መጽሄት | ጋዜጣ | የሃይማኖት መጻህፍት |
| ድምር<br>% | 28<br>39.2 | 27<br>37.8 | 21<br>29.4 | 18<br>25.2 |
| 5 | ከላይ ከተዘረዘሩት ብዙ የምታነበው/ቢው | | | |
| ድምር<br>% | 25<br>36.4 | 19<br>26.6 | 13<br>18.2 | 14<br>19.6 |

በጥያቄ ቁጥር 4 ላይ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ከአጠቃለይ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ቁጥር በላይ ነው፡፡ ማለትም መጠይቁን የሞሉት 76 ተማሪዎች ሲሆኑ የተገኘው ውጤት ድምር የ96 ተማሪዎች (131.6%) ነው:: ይህ የሆነበት ምክንያትም ከአንድ በላይ የሆነ መልስ የሠጡ ተማሪዎች በመኖራቸው ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ መጽሄት እና ጋዜጣ መጨመራቸው በጥያቄ ቁጥር 8 ላይ የተገኘውን ውጤት ጎደሎ አያደርገውም፡፡ ምክንያቱም በጥያቄ ቁጥር 5 ላይ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ሁለቱ መጻህፍት ሲሆኑ ብዙ የመነበብ እድልም ያገኙት እነሱ ናቸው፡፡ ከግማሽ በላይ የሆነውን ማለትም 56% የሚሆነውን ብዙ የመነበብ እድል ያገኙት መጻህፍት መሆናቸው በመጻህፍት ቁጥር የተደረገውን ምዘና ተገቢነት ያረጋግጥልናል፡፡ በሰንጠረዥ ላይ እንደሚታየው መጽሄት እና ጋዜጦች በከፍተኛ ደረጃ 37.8% እና 29.4% የሆነ ተመራጭነት አላቸው፡፡ ይሁንና መጽሄት እና ጋዜጣ በየወቅቱ የሚወጡ በመሆናቸው ይህን ያህል አንብቤያለሁ ብሎ ለመናገር ስለሚያስቸግር በቁጥር 8 ጥያቄ ምርጫ ውስጥ አልገቡም፡፡

### 3.1.3. ተማሪዎች ትምህርት ነክ ስላልሆኑ ጽሁፎች ያላቸውን ግንዛቤ ትንተና

ሰንጠረዥ 4፡- ተማሪዎች ስለንባብ ያቸውን አመለካከት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| | ጥያቄዎች | አማራጮች | ብዛት | % |
|---|---|---|---|---|
| 6 | ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የምታነብ ከሆነ የምታነበው/ቢው ለምን አላማ ነው? | ሀ. ለጠቅላላ እውቀት<br>ለ. ጊዜ ለማሳፍ<br>ሐ. የንባብ ልምድን ለማዳበር | 49<br>8<br>11 | 68.6<br>11.2<br>15.4 |
| | | ለ እና ሐ<br>ለሶስቱም | 1<br>2 | 1.4<br>2.8 |
| 7 | ከመማሪያ መጻሀፍት ውጭ የሆኑ ጽሁፎችን ማንበብ ለምን ይጠቅማል ብላችሁ ታስባላችሁ? | ሀ. ለጠቅላላ እውቀት<br>ለ. ለስነ-ፅሁፍ እውቀት<br>ሐ. በትምህርት ውስጥ ትምህርት የተሻለ እውቀት ለማሳካት<br>መ. ሌላ ጥቅም ካለ | 35<br>4<br>5<br>27 | 45<br>5.6<br>7<br>37.8 |

ከዚህ ሰንጠረዥ እንደምንረዳው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተማሪ ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ አላማ ጠቅላላ እውቀት ለማግኘት ነው የሚል ግንዛቤ ነው ያለው፡፡ 11.2% ተማሪ ብቻ ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ አላማ ለጊዜ ማሳለፊያ ነው የሚል ግንዛቤ መያዙ በጥያቄ ቁጥር 3 ላይ የተማሪዎችን በትርፍ ጊዜያቸው ንባብን በመዝናኛነት የመጠቀምን አናሳነት አስመልክቶ የሰጠውን ማጠቃለያ ያጠናክራል፡፡ 15.4% ተማሪዎች ደግሞ ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ አላማ የንባብ ልምድን ለማዳበር ነው የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡

ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብን ጠቀሜታ አስመልክቶ 59.6% ተማሪዎች ከቀረቡላቸው አማራጮች መካከል ሲመርጡ 37.8% ደግሞ ሌሎች ጠቀሜታዎችን ዘርዝረዋል፡፡ 45% ለጠቅላላ እውቀት፣ 5.6% ለስነ ጽሁፍ እውቀት፣ 7% ደግሞ በክፍል ውስጥ ትምህርት የተሻለ እውቀት ለማካበት ሲሉ መርጠዋል፡፡ ሌላ

ጥቅም ካለ በሚለው ውስጥ ከተሰጡት መልሶች መካከል ለመዝናናት የሚለው 8.4% በማግኘት ከፍተኛውን ድርሻ ሲይዝ የህይወት ተሞክሮ ለማግኘት፣ ችግሮችን ለመፍታት፣ አስተሳሰብን ለማስፋት፣ አዲስ እውቀት ለማግኘት፣ በሀይማኖት ለመጽናት፣ ራስን ለመፈለግ ወዘተ … የሚሉ መልሶች ሰጥተዋል፡፡

### 3.1.4. የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች የማንበብ ልምድ ላይ አስተዋጽኦ ያደረጉ አካላት

ሰንጠረዥ 5፡- የንባብ ልምድ ላይ አስተዋጽኦ ያደረጉ አካላት ያላቸውን ድርሻ የሚያሳይ

| | ጥያቄ | አማራጮች | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| 9 | በጥያቄ ቁጥር 8 ለተጠቀሰው ጥያቄ መልስህ ከ "መ " ሌላ ከሆነ የንባብ ልምድህን ከፍተኛ እንዲሆን አስተዋጽኦ ያደጉት አካላት እነማን ናቸው? | ሀ. ቤተሰቦቼ<br>ለ.ትምህርት ቤት<br>ሐ. ጓደኞቼ<br>መ. ሌላ ካለ ይግለጹ | 18<br>6<br>4<br>10 | 46.15<br>15.36<br>10.24<br>28.26 |

የዚህ ጥያቄ መልስ የተወሰደው የንባብ ልምዳቸው ከ10 መጻህፍት በላይ ከሆነ 39 ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ውጤቱ እንደሚያሳየው 46.15% የሚሆኑት ተማሪዎች አሁን ያላቸውን ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ የያዙት በቤተሰቦቻቸው እገዛ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶች 15.36% የሆነ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ተገልጿል፡፡ ከውጤቱ እንደሚታየው የትምህርት ቤቶች አስተዋጽኦ አነስተኛ ነው፡፡ ይህም የተባለበት ምክንያት ትምህርት ቤቶች የንባብ ልምድንም ሆነ ሌሎችን ጠቃሚ የሚባሉ ልምዶችን በማዳበር ረገድ የተሻለ አስተዋጽኦ ሊኖራቸው ይገባል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ 10.24% ተማሪዎችን ጓደኞቻቸውን ሲጠቅሱ ሌላ ጥቅም ካለ ይግለጹ በሚለው ላይ 17.92% ራሳቸው ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምዳቸው እንዳዳበሩ ገልጸዋል፡፡

ሰንጠረዥ 6፡- በትርፍ ጊዜያው የተማሪዎች ለንባብ ያለ ተነሳሽነት

| በትርፍ ጊዜህ የንባብ ልምድን ለማዳበር ጥረት ታደርጋለህ? | |
|---|---|
| ሀ. አደርጋለሁ | ለ. አላደርግም |
| 87.77 | 12.23 |

በጥያቄ ቁጥር 10 ለተማሪዎች የቀረበላቸው ጥያቄ በትርፍ ጊዜህ የንባብ ልምድን ለማዳበር ጥረት ታደርጋለህ ወይስ አታደርግም የሚል ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ በመጠይቁ ውስጥ የተሳተፉ የሁሉም ተማሪዎች "ምንም አላነብም" የሚል መልስ የሰጡትም ጭምር ያካተተ ነው፡፡ በዚህም መሰረት 87.77% ተማሪዎች በትርፍ ጊዜዬ የንባብ ልምድን ለማዳበር ጥረት አደርጋለሁ ሲሉ 12.23% ደግሞ ጥረት አላደርግም ብለዋል፡፡ ይሁንና በጥያቄ ቁጥር 3 ላይ ትርፍ ጊዜያቸውን በምን እንደሚያሳፉ ለተጠየቁት ጥያቄ 28% ተማሪዎች ብቻ በንባብ እንደሚያሳፉ መግለጻቸውን ስናይ ይህን ምላሽ እንጠራጠራለን፡፡ ምክንያቱም አስቀድሞ የሌለ ነገር ሊዳበር ስለማይችል ነው፡፡ በትርፍ ጊዜዬ የንባብ ልምድን ለማዳበር ጥረት አላደርግም ያሉ ተማሪዎች አላደርግም ያሉበትን ምክንያት ሲገልጹ አብዛኞች ፍላጎት እና ትኩረት የለኝም ሲሉ ሌሎቹ አስቀድሞም ያን ያህል የንባብ ልምድ ስለሌለኝ ብለዋል፡፡ የቀሩት ደግሞ ከጥናት የሚተርፋቸውን ሰአት በሌሎች የመዝናኛ መንገዶች ሊያሳልፉ ስለሚፈልጉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

### 3.2. የየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት የቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ ትንተና

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በሞሉት መጠይቅ የወሰጡትን ምላሽ መምህራን በሰጡት ምላሽ ላይ ተመርኩዘን ለማጋገጥ እንሞክራለን፡፡

መጠይቁን የሞሉት መምህራን አጠቃላይ መረጃ

| ፆታ | | የት.ደረጃ | | የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት | | የአገልግሎት ዘመን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | ሴ | BA | MA | አማርኛ | እንግሊዝኛ | ከ5-15 | ከ15-30 | ከ30 በላይ |
| 4 | 2 | 5 | 5 | 2 | 4 | 4 | 1 | 1 |
| 66.4% | 33.6 | 50 | 50 | 33.6 | 66.4 | 66.4 | 16.6 | 16.6 |

ሰንጠረዡ እንደሚያሳየው በመጠይቁ ከተካተቱት መምህራን 66.4% ወንዶች ሲሆኑ 33.6% ሴቶች ናቸው። 50% በቋንቋ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን 50% ደግሞ የሁለተኛ ዲግሪ ያቸው ናቸው። 66.4% የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ሲሆኑ 33.6% የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። የእንግሊዝኛ መምህራን ቁጥር የመብዛቱ ምክንያቱም መጠይቁ በሚሞላበት ወቅት በብዛት የተገኙት እነርሱ ስለነበሩ ነው። 16.4% በማስተማር ሙያ ውስጥ ከ30 አመት በላይ የቆዩ ሲሆን 66.4% ከአምስት እስከ አስራ አምስት አመት በዚሁ ሙያ ውስጥ ቆይተዋል። 16.6% ደግሞ ከአስራ አምስት እስከ 30 አመት የስራ ልምድ አላቸው።

### 3.2.1. ንባብ እና የቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በመምህራን እይታ

ሰንጠረዥ 7፦ የንባብ ድርሻ በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለሚያስተምሩበት ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት በአብዛኛው የሚያተኩረው በየትኛው ክሂል ላይ ነው | | | |
| ሀ. በማዳመጥ | ለ. በመናገር | ሐ. በማንበብ | መ. በመጻፍ |
| 4<br>66.6 | 3<br>49.8 | 3<br>49.8 | 5<br>83 |
| በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የተማሪዎች የማንበብ ልምድ እንዲሻሻል ያለው አስተዋጽኦ | | | |
| እጅግ በጣም ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | ዝቅተኛ |
| 2 | 2 | 1 | 1 |
| 33.6 | 33.6 | 16.6 | 16.6 |

መምህራኑ በክፍል ውስጥ የሚሰጡት ትምህርት በአብዛኛው ምን ላይ እንደሚያተኩር ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ ውጤት መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ቁጥር ይበልጣል። ይህም የሆነበት ምክንያት ሶስት መምህራን በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት በሁሉም ክሂሎች ላይ ያተኩራል በማለታቸው ነው። በአጠቃላይ ስናየው 83% በመጻፍ 66.6% በማዳመጥ 49.8 በመናገር 49.8 በማንበብ

ላይ ያተኩራል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት እንደ መምህራኑ ምላሽ በይበልጥ በመጻፍ እና በማዳመጥ ላይ ያተኩራል፡፡ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን አብዛኞቹ የእግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን በመሆናቸው እና ትምህርቱ የሚሰጠው በቴሌቪዥን በመሆኑ በዚያ ላይ በብዛት ሊስተዋል የሚችለው ነገር መጻፍና ማዳመጥ በመሆኑ ነው የሚል ግምት አለ፡፡

መምህራኑ በክፍል ውስጥ የሚሰጡት ትምህርት የንባብ ልማድ እንዲሻሻል ያለው አስተዋጽኦ ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ 33.6% እጅግ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አለው ሲሉ፣ 33.6% በጣም ከፍተኛ፣ 16.6% ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡ 16.6% ብቻ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ዝቅተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡ ይህ የመምህራኑ ምላሽም ተማሪዎች በሞሉት መጠይቅ ጥያቄ ቁጥር 9 ላይ የንባብ ልምዳቸው እንዲዳብር የትምህርት ቤት አስተዋጽኦ ዝቅተኛ (15.36%) ነው ብለው ከሰጡት መልስ ጋር የሚጋጭ መሆኑ የመምህራኑ ምላሽ ላይ ጥያቄ እንድናነሳ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የእንግሊዝኛ ትምህርት በቴሌቭዢን የሚሰጥ በመሆኑ ከንባብ ይልቅ የማድመጥ ክሂልን ለማዳበር የተሻለ እድል አለው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትንም በሚመለከት ብናይ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ሲሆን በእነዚህ ክፍለ ጊዜያትም አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች ማስተማር የሚገባቸው በመሆኑ የክፍል ውስጥ ትምህርቱ የንባብ ክሂል እንዲዳብር  እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ማለታቸውን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡ ስለዚህም መምህራን በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የንባብ ልምድ እንዲሻሻል ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ብለው የሚሠጡትን ምላሽ አጠራጣሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህን የመምህራኑ ምላሽ የበለጠ ለማጣራት በመምህራኑ የተማሪዎችን ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ በተመለከተ ያላቸውን አስተያየት ተጠይቀው የሰጡትን ምላሽ መመርመር ያሻል፡፡

መምህራኑ በጥያቄ ቁጥር 5 ላይ የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ ምን ያህል ነው ተብለው ለተጠየቁት 33.6% በጣም ከፍተኛ ነው 16.6% መካከለኛ፣ 33.6% ዝቅተኛ፣ 16.6% ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ የምንረዳው 66.4% የሚሆኑት ተማሪዎች ተገቢ የሆነ የንባብ

ልማድ እንደሌላቸው ነው፡፡ መምህራኑ በጥያቄ ቁጥር 2 እና በጥያቄ ቁጥር 5 በሰጧቸው መልሶች መካከል የሚታይ መጣረስ አለ፡፡ ይህም በቁጥር 2 ላይ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የንባብ ልምድ እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ሲሉ በቁጥር 5 ላይ ደግሞ የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች የማንበብ ልምድ ዝቅተኛ ነው የሚል ነው፡፡

ይሁንና 88.2% የሚሆኑት ተማሪዎች ከ30 መጻህፍት በታች ያነበቡ መሆናቸውን ስናይ፤ ተማሪዎች ትምህርት ቤቶች የንባብ ልምዳቸው እንዲዳብር ያደረጉላቸው አስተዋጽኦ 15.36% ብቻ መሆኑን ስናስተውል እና እራሳቸው መምህራኑ በጥያቄ ቁጥር 5 ላይ የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ ዝቅተኛ ነው ማለታቸውን ስናገናዝብ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የንባብ ልምድ እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ብለው የሰጡትን መልስ አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ ዝቅተኛ ወይም በጣም ዝቅተኛ የሚል መልስ ለሰጡት መምህራን ምክንያቱ ምንድን ነው ተብለው ያስባሉ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ አንዱ መምህር የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት አለመኖር ነው ሲሉ ሌላው መምህር ደግሞ በክፍል ውስጥ በሚሰጠው የንባብ ትምህርት ላይ ትኩረት አለመደረጉ ነው ብለዋል፡፡ በጥያቄው ውስጥ ለተማሪዎች የንባብ ልምድ ማነስ ምክንያት ይሆናሉ ተብለው የቀረቡት በብዛት የሚነበቡ ጽሁፎች አለመገኘት እና የማንበቢያ ቦታ እጥረት በመምህራኑ እንደ ምክንያት አለመመረጡ የሚያሳየው አጥኚው በተማሪዎች መጠይቅ ጥያቄ ቁጥር 2 ላይ እነዚህን አማራጮች የሠጡትን ተማሪዎች አስመልክቶ ከሰጠው ድምዳሜ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ማለትም በጥያቄ ቁጥር 1 ላይ የንባብ ልምዳችን ዝቅተኛ ወይም 'ምንም አላነብም' ያሉት ተማሪዎች በጥያቄ ቁጥር 2 ላይ ምክንያታቸውን ሲጠይቁ የተወሰኑት በማንበቢያ ቦታ እና በመጻህፍት እጥረት ብለው የሰጡትን ምላሽ አጥኚው ት/ቤቱ የሚገኝበትን ቦታ እና የተማሪዎች በዚያው አቅራቢያ መገኘት አስገንዝቦ አልተቀበለውም፡፡ በዚህ ምላሽ ላይም የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ ዝቅተኛ ወይም በጣም

ዝቅተኛ ያሉ መምህራን ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሲጠየቁ እነዚህን ምክንያቶች አለመጥቀሳቸው የአጥኚውንና የመምህኑን ድምዳሜ ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡

### 3.3.2. የተማሪዎች የንባብ ልምድ በመምህራን እይታ

ሰንጠረዥ 8፡- የተማሪዎች የንባብ ልምድ በመምህራን እይታ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከሚያስተምሩአቸው ተማሪዎች የተሸለ የማንበብ ልምድ ያላቸው የትኞቹ ናቸው? | | | |
| ሀ. ወንዶች | | ለ. ሴቶች | |
| 2<br>33.6 | | 4<br>66.4 | |
| በእርስዎ አስተያየት የተማሪዎች የንባብ ልምድ ከምን ጋር የተያያዘ ነው? | | | |
| ሀ. ጊዜ ከማሳለፍ | ለ. ከመዝናናት | ሐ. ጠቅላላ እውቀት ከማግኘት | መ. የንባብ ልምድን ከማዳበር |
| 2<br>33.4 | 2<br>33.4 | 1<br>16.6 | 1<br>16.6 |

መምህራኑ ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች የተሸለ የማንበብ ልምድ ያላቸው የትኞቹ ናቸው ለሚለው ጥያቄ 66.4% ሴቶች ናቸው ሲሉ 33.6% ወንዶች ናቸው ብለዋል፡፡ በቀጣዩ ጥያቄ የተማሪዎች የንባብ ልምድ ከምን ጋር የተያያዘ ነው ብለው ያስባሉ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 33.4% ጊዜ ከማሳለፍ 33.4% ደግሞ ከመዝናናት ጋር የተያያዘ ነው ብለዋል፡፡ የተሻለ የማንበብ ልማድ ያላቸው ሴቶች ናቸው የሚል መልስ ስለተሰጠ ቀጥሎ የተሰጠው መልስ ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም አብዛኞዎቹ ሴቶች ከት/ቤት መልስ ቤት ውስጥ ስለሚያሳልፉ ለጊዜ ማሳለፊያነት እና ለመዝናኛነት ፊልም ከማየት እና ሙዚቃ ከመስማት ቀጥሎ ንባብን ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ነው፡፡ ይሁንና ተማሪዎች ንባብን ጠቅላላ እውቀት ለማግኘት እንደሚጠቀሙበት ከሰጡት መልስ ጋር ይህ መልስ ይጋጫል፡፡

### 3.3.3. የንባብ ልምድን በማሳደግ ረገድ ያለ ድርሻን አስመልክቶ መምህራን የሰጡት ምላሽ

ሰንጠረዥ 9፡- የተማሪዎች የንባብ ልምድ ላይ የመምህራን እና ሌሎች አካላት ድርሻ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | በተማሪዎች የማንበብ ልምድ ላይ የበለጠ አዎንታዊ ተጽእኖ አለው የሚሉት ማንን ነው? | | | | |
| | ሀ. ቤተሰብ | ለ. ትምህርት ቤት | ሐ. የሚኖሩበት አካባቢ | መ. መምህራን | ሠ. ሁሉም |
| | 1 | | | | 5 |
| | 16.6 | | | | 83.4 |
| 10 | ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን እንዲያነቡ ያበረታታሉ? | | | | |
| | ሀ. አበረታለሁ | | ለ. አላበረታታም | | |
| | 6<br>100% | | -<br>- | | |

ለጥያቄ ቁጥር 7 በሰጡት ምላሽ 16.6% ቤተሰብ የበለጠ አዎንታዊ ተጽእኖ አለው ሲሉ 83.4% ሁሉም አካላት ተጽእኖ መፍጠር ይችላሉ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን እንዲያነቡ ያበረታሉ በሚለው ጥያቄ 100% አበረታታለሁ ብለዋል፡፡ በምን አይነት መንገድ እንደሚያበረታቷቸው ተጠይቀው፡፡ 50% መምህራኑ ተማሪዎች ከሌሎች ነገሮች አንብበው እንዲመጡ የቤት ስራ በመስጠት 33.4% የተለያዩ ጽሁፎችን እንዲያነቡ በማበረታታት፣ 16.6% ደግሞ የማስተማር ሂደቱ ሁሉንም የቋንቋ ክህሎቶች በሚያዳብር መልኩ በማስኬድ ብለዋል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ግማሽ ያህሉ መምህራን ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን ማስነበብን በማስተማር ሂደታቸው ውስጥ አካተውታል፡፡ አጥኚው ይህን አካሄድ ተገቢ ነው ይላል፡፡ ሁሉም መምህራን በማስተማር ሂደታቸው ወቅት ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የሚያነቡበትን መንገድ ማመቻቸት ከማበረታትም በዘለለ በተወሰነ መልኩ የቤት ስራዎችንና ፈተናዎችን በመስጠት ግፊት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን በጥያቄ ቁጥር 5 ላይ 50% የሚሆኑ መምህራን

የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ ዝቅተኛ ነው ማለታቸው እና ለዚህ ጥያቄ ደግሞ 100% አበረታታለሁ ማለታቸውን ስናይ የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ ዝቅተኛ ነው ብለው መልስ የሰጡት መምህራን ለዚህ ጥያቄ የሰጡትን አበረታታለሁ የሚል ምላሽ አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም እንዲያነቡ ማበረታቻ የሚደረግላቸው ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸው ዝቅተኛ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ አነስተኛ ስለሆነ ነው፡፡

ለመምህራኑ በመጨረሻ የቀረበው ጥያቄ  የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ እንዲሻሻል ምን ሊደረግ ይገባል ይላሉ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ሳቢነት ያላቸው እና ከእድሜያቸው ጋር የሚሄዱ ጽሁፎች ቢዘጋጁ፣ ማበረታቻ ሽልማቶች ቢኖሩ፣ የማንበብ ልምድ እንዲይዙ ቢበረታቱ፣ ቅስቀሳ ቢካሄድ፣ ያነበቡትን ነገር በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ቢደረግ፣ የንባብ ክፍል ቢዘጋጅ ወዘተ የሚሉ ምላሾችን ሰጥተዋል፡፡ ይህ የመምህራኑ አስተያየት ሚያመለክተው እስካሁን የንባብ ልምድን በማሻሻል ረገድ በተለይም ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽኑፎችን የማንበብ ልምድ በማሳደግ ረገድ ሊሰራ የሚገባው ስራ በአግባቡ እንዳልተከናወነ ነው፡፡ ምክንያቱም ተገቢው ስራ ተሰርቶ ቢሆን ኖሮ በጥናቱ አዎንታዊ ውጤት ይገኝ የነበረ ሲሆን መምህራኑም እነዚህን በመሰረታዊነት ሊሰሩ የሚገባቸውን ነገሮች እንደ አዲስ በጥቆማ መልክ ሊያቀርቡ አይችሉም ነበር፡፡

## ምእራፍ አራት

## ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

### 4.1. ማጠቃለያ

ቀደም ሲል በምእራፍ አንደ ላይ እንደተገለጸው ይህ ጥናት የየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት የተማሪዎችን ትምህርት ነክ ያልሆኑ ፅሁፎች የማንበብ ልምድ መመዘን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ የተከናወነው በናሙና የተመረጡ ተማሪዎችን እና መምህራንን የፅሁፍ መጠይቅ በማስሞላት ሲሆን በዚህ መሰረት የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አሳይቷል፤ ትምህርት ነክ ስላልሆኑ ጽሁፎች ያላቸውን አተያይ ፈትሿል፤ የማያነቡ ተማሪዎች ያለማንበብ ምክንያታቸው ምን እንደሆነ አጣርቷል፡፡ ከዚህም በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ከተደረገው ጥናት በኂላም የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

- ተማሪዎች ራሳቸው የንባብ ልምዳቸውን አስመልክቶ ከሰጡት ምላሽ እና ካነበቧቸው መጻህፍት ቁጥር አንጻር እንደታየው ከትምህርታቸው ውጭ የሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምዳቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ታውቋል፡፡
- አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች ማንበብ አላማም ሆነ ጠቀሜታ ለጠቅላላ እውቀት ነው ብለው የሚያምኑ ሲሆኑ ከዚያ ለተለየ አላማ ብለው የሚያነቡ ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ ነው፡፡ ይሁንና ንባብ ዘርፈ ብዙ አላማ እና ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ተማሪዎች ግን በጣም ጥቂቱን እንደሚያውቁ ታይቷል፡፡
- ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው ከማንበብ ይልቅ ሌሎች ተግባራትን ማለትም እንደ ፊልም ማየት፣ የእግር ጉዞ ማድረግ፣ ኳስ መጫወት እና ኳስ ማየት ወዘተ… በማከናወን ያሳፋሉ፡፡ ይህም ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች በትርፍ ሰአት የሚነበቡ እንደመሆናቸው መጠን እነርሱን በማንበብ ረገድ ሊኖር የሚገባው ልማድ ሊዳብር እንዳይችል እንዳደረገ ታይቷል፡፡
- የተማሪዎችን የንባብ ልምድ በማዳበር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ አካላት ማለትም ቤተሰብ፣ ት/ቤት፣ ማህበረሰቡ የሚጠበቀውን ያህል ተጽእኖ መፍጠር ያልቻሉ ሲሆን በተለይም በትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎች አንጻር ያላቸው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

## 4.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

ከዚህ ጥናት አላማዎች መካከል አንዱ በምእራፍ ሶስት ለተጠቀሱት ችግሮች የመፍትሄ ሃሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ በአጥኚው የታመነባቸው እንዳንድ ሀሳቦች ማቀበል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ሶስት የመፍትሄ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ እነርሱም የንባብ ክፍል ማዘጋጀት፣ ቅስቀሳ ማካሄድ እና ሳቢነት ያላቸው ጽሁፎች በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ማካተት ናቸው፡፡

የንባብ ክፍል ማዘጋጀት ሲባል ካሉት የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች ውስጥ ለንባብ መደበኛ የሆነ ክፍለ ጊዜ መስጠት ማለት ነው፡ በዚህ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ አይነት ጽሁፎችን እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲለምዱት እና እንዲወዱት ማድረግ ይቻላል፡፡ ሌላው የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በተለይም ለተማሪዎች ቅርበት አላቸው የሚባሉትን በመጠቀም ቅስቀሳ ማካሄድ በጣም ጠቀሜታ ያለው ተግባር ነው፡፡ የመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት በሚካሄድበት ወቅት በተለይም የቋንቋ ትምህርት መጻኅፍት ዝግጅት በሚካሄድበት ወቅት የተማሪዎችን ፍላጎት ያገናዘቡና ሳቢነት ያላቸው ጽሁፎች በመጻህፍት ውስጥ ማካተትም ተማሪዎች የንባብ ፍላጎታቸው እንዲዳብር የማድረግ ችሎታቸው ከፍ ያለ ነው፡፡

በአጠቃላይ ስናየው የንባብ ልምድን በተለይም ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድን ለማዳበር የሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አስፈላጊ ነው፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ክፍል ትምህርት

በየካቲት 12 የመሰናዶ ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ አላማ በየካቲት 12 የመሰናዶ ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ መመዘን ነው፡፡

ጥናቱ የታቀደለትን ግብ ይመታ ዘንድ ትክክለኛ መረጃ መሠብሰብ አስፈላጊ በመሆኑ መጠይቁ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክለኛ መልስ እንድትሰጡ አጥኚው በአክብሮት እየጠየቀ ለሚደረግለት ትብብር በቅድሚያ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ጾታ ________ እድሜ____________ የክፍል ደረጃ_____________

የትምህርት ዘርፍ ማህበራዊ ሳይንስ ☐ ተፈጥሮ ሳይንስ ☐

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ ናቸው የምትሉዋቸውን መልሶች መርጣችሁ በማክበብና ተጨማሪ ማራሪያ ካለም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመጻፍ መልስ ስጡ

1. ከመደበኛ የመማሪያ መጻህፍት ውጭ ያሉ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድህ/ሽ ምን ያህል ነው?

   ሀ. በጣም ከፍተኛ ለ. ከፍተኛ ሐ. ዝቅተኛ መ. ምንም አላነብም

2. በተራ ቁጥር 1 ላይ ለቀረበው ጥያቄ መልስህ "ሐ" ወይም "መ" ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው ትላለህ/ትያለሽ

   ሀ. ፍላጎት ስለሌለኝ ለ. ግዜ ስለሌለኝ ሐ. በማበቢያ ቦታ እጥረት

   መ. በመጻህፍት እጥረት

3. ትርፍ ጊዜህን በምን ታሳልፋለህ/ታሳልፊያለሽ

   ______________________________________________

4. ትምህርት ነክ የሆኑ ፅሁፎችን የምታነብ ከሆነ ምንድነው የምታነበው?

   ሀ. ልቦለድ ለ. መጽሄት ሐ. ጋዜጣ መ. የሀይማኖት መጻህፍት

5. ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ብዙ የምታነበው/ቢው የትኛውን ነው?

   ______________________________________________

6. ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የምታነብ ከሆነ የምታነበው/ቢው ለምን አላማ ነው?

ሀ. ጊዜ ለማሳፍ ለ. የንባብ ልምድን ለማሻሻል ሐ. ለጠቅላላ እውቀት

7. ከመማሪያ መጻኅፍት ውጭ የሆኑ ጽሁፎችን ማንበብ ለምን ይጠቅማል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ሀ. ለጠቅላላ እውቀት ለ. ለስነጽሁፍ እውቀት ሐ. በክፍል ውስጥ ትምህርት የተሻለ እውቀት ለማካበት

ሌላ ጥቅም ካለ ግለጽ______________________________________

8. እስካሁን በግምት ምንያህል መጻህፍት አንብበሀል/ሻል?

ሀ. ከ 30 በላይ ለ. ከ20-30 ሐ. ከ10-20 መ. ከ10 በታች

9. በጥያቄ ቁጥር 8 ለተጠቀሰው ጥያቄ መልስህ ከ "መ" ሌላ ከሆነ የንባብ ልምድህ ከፍተኛ እንዲሆን አስተዋጽኦ ያደረጉ አካላት እነማን ናቸው?

ሀ. ቤተሰቦቼ ለ. ትምህርት ቤት ሐ. ጓደኞቼ መ. ሌላ ካለ ይግለጹ______

____________________________________________________________

10. በትርፍ ጊዜህ የማንበብ ልምድን ለማዳበር ጥረት ታደርጋለህ?

ሀ. አደርጋለሁ ለ. አላደርግም

11. በተራ ቁጥር 10 ለቀረበው ጥያቄ መልስህ አላደርግም ከሆነ ምክንያቱ ይገለጽ______

____________________________________________________________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ክፍል ትምህርት

በየካቲት 12 የመሰናዶ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ አላማ በየካቲት 12 የመሰናዶ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ መመዘን ነው፡፡

ጥናቱ የታቀደለትን ግብ ይመታ ዘንድ ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ በመሆኑ መጠይቁ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክለኛ መልስ እንድትሰጡ አጥኚው በአክብሮት እየጠየቀ ለሚደረግለት ትብብር በቅድሚያ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ፆታ_______________

የትምህርት ደረጃ______________________

የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት________________

የአገልግሎት ዘመን______________

የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ___________

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ ናቸው የምትሏቸውን መልሶች መርጣችሁ በማክበብ ተጨማሪ ማብራሪያ ካለም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመጻፍ መልስ ስጡ፡፡

በሚያስተምሩበት ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት

1. በአብዛኛው የሚያተኩረው በየትኛው ክሂል ላይ ነው?

   ሀ. በማዳመጥ ለ. በመናገር ሐ. በማንበብ መ. በመጻፍ

2. በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የተማሪዎች የማንበብ ልምድ እንዲሻሻል ያለው አስተዋጽኦ

   ሀ. እጅግ በጣም ከፍተኛ ለ. በጣም ከፍተኛ ሐ. ከፍተኛ መ. ዝቅተኛ

3. ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን እንዲያነቡ ያረታታሉ?

   ሀ. አበረታታለሁ ለ. አላበረታም

4. መልስዎ አበረታለሁ ከሆነ በምን አይነት መንገድ________________________

________________________________________________________________

5. በእርስዎ አመለካከት የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ

ሀ. በጣም ከፍተኛ ለ. ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ

መ. ዝቅተኛ ሠ. በጣም ዝቅተኛ

6. ለተራ ቁጥር 5 መልስዎ "መ" ወይም "ሠ" ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው ይላሉ?

ሀ. ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መብዛት ለ. በብዛት የሚነበቡ ጽሁፎች አለመገኘት

ሐ. የማንበቢያ ቦታ እጥረት መ. ሌላ ምክንያት ካለ ይግለጹ ______________

________________________________________________________________

7. በተማሪዎች የማንበብ ልምድ ላይ የበለጠ አዎንታዊ ተጽእኖ አለው የሚሉት ማንን ነው?

ሀ. ቤተሰብ ለ. ትምህርት ቤት

ሐ. የሚኖሩበት አካባቢ መ. መምህራን ሠ. ሁሉም

8. ከሚያስተምሩአቸው ተማሪዎች ተሻለ የማንበብ ልምድ ያላቸው የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ወንዶች ለ. ሴቶች

9. በእርስዎ አስተያየት የተማሪዎች የንባብ ልምድ ከምን ጋር የተያያዘ ነው?

ሀ. ጊዜ ከማሳለፍ ለ. ከመዝናናት

ሐ. ጠቅላላ እውቀት ከማግኘት መ. የንባብ ልምድን ከማዳበር

10. የተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድ እንዲሻሻል ምን ማደረግ ይገባል ይላሉ?________________________________

________________________________________________________________

## ዋቢ መጻኅፍት

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1986)፡፡ <u>አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ማዳበር</u>
አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ብርቱካን እሸቱ፡፡ (1993)፡፡ "የንባብ ልምድ ከጽህፈት ክሂል ጋር ያለው ዝምድና፤ በ2ኛ ዓመት የኢትዮጵያ ቅንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የማታ የዲፕሎማ መርሀ ግብር ተማሪዎች ላይ እንደተሞከረው"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ /ያልታተመ/

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ <u>በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር</u>
አዲስ አበባ, ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አያሌው ታዬ፡፡ (1999፡፡ "የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂልን በማዳበር ረገድ የቡድን ንባብ ፋይዳ በየካቲት 12 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና አጠቃላይ የመሰናዶ ት/ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ /ያልታተመ/

Aebersold, J. Ann & Mary.L.F (1997). <u>From Reader to Reading teacher.</u>
New York: Cambridge university press

Brooks. N (1964). <u>Language and Language teaching</u>.
New Haven: Connecticut, Harcovrt, Brace and world Inc

Byme.D.(1991). <u>Teaching writing Skills</u>.
Hong Kong: Longman Group (FE)LTD.

Morris, R. (1979). <u>Success and Failure in Learning to read.</u>
Harmondworth: penguin books.

Grellet.F. (1981). <u>Developing Reading skill.</u> London: Cambridge University press.

McGarry.K. (1991). <u>Literacy, Communication and Libraries.</u>
London: Library association publishing.

Nuttal,C. (1982). <u>Teaching reading skills in a foreign language.</u>
London: Heina maan Educational books.

Taylor,T. (1973). Reading and writing in first school. London: Cambridge University press.

Troyka, L-Q. (1990). Simon and schuster word book for writers. New Jersey: Prentice Hall.

Leadrach. J.P. (1995). Preparing for peace, conflict transformation across cultures. Syracuse, NY: syracuse university press.

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. “Yet there are signs that even in the so called advanced industrialized nations there are disturbing signs of declining litracy and also a declining in the reading habit. A recent Survey by the Scotish arts council revealed that only one in 15 fifteen year olds reads for more than three hours week, where as television viewing averages a weakly 14 hours”
2. “Reading is not a passive acticity. It involves more than looking at words. Reading is an active process. A dynamic meaning making encounter involving the interaction of the page. Eye and brain, when you read your mind makes connection among what you already know, what you are currently learning and what is new to you.
3. Further more a child who can’t read is necessarily a child who can’t write. So that and kind of creative or factual writing is barred to the non read child.
4. Extensive reading:- Longer text, usually for once own pleasure (This is a fluency activity involving global understanding)
5. By intensive reading we mean the careful study.
6. Homes that are filled with magazines news papers and books send a clear message to children about the value of reading.
7. In schools where there is active promotion of the reading habit and where plenty of enjoyable easy books are available it is not at all unusual to find students reading a book a week and many read more than this.
8. Culture has been defined in a number of ways, But most simply, as the learned and shared behavior of a community of interacting human beings.
9. While different social and economic groups with in a culture may emphasize different uses for reading, over arching culture value

shape the general attitudes toward reading that a cultural group shares.

10. Readability is not a matter only of grammatical complexity and lexical difficulty.

11. Of all the qualities above, exploitability is arguably the most important after interest.

12. Students who read slowly will easily get discouraged

13. By reading all texts in the same way, students would waste time and fail to remember points of importance to them because they would absorb too-much non essential information

14. You will need to look at possible materials from three points of view readability, suitability of content and exploitability.

15. H.D.Brown (1987, 101-115) details several individual factors that influense language learning including self esteem, inhibition, risk taking, anxiety, and motivation. All of these factors operates in the reading classroom as well

16. Reading will play an extremely important part in the dev't of writing ability because of although in it self it will not produce good writers it appears to an essential pre-condition.

17. Functional reading- includes all types of reading in which the primary aim is to obtain information, in other words reading to learn, some writers prefer to call it study type reading or work type reading.

    Developmental reading- Activities are those in which the main purpose of the teacher is to bring about an important in reading skill activities in which learning to read is the main goal.

    Recreational reading- Consists of those reading activities which have enjoyment, entertainment and appreciation as major purpose.

18. Reading for literal meaning:- Calls for you to understand what is said. It does not include impression or opinions about the material.

Reading to make inference:- means understanding what is implied but not stated often you have to infer information, or background or the authors purpose.

Reading to Evaluate - calls for many skills including recognizing the impact of the authors tone, detecting prejudice and differentiating fact from opinion.

19. when skimming we go through the reading material quickly in order to get the gist of it, to know how it's organized or to get an idea of the forme or the intention of the writer

20. When scanning, we only try to locate specific information and often we do not follow the linearity of the passage to do so we simply let our eyes wonder over the text until we find what we are looking for whether it be a name, a date or a less specific piece of information.

22. Subvocalizing- If you subvocalize you will tend to read word by word instead of in sense group and it will be difficult to improve your speed. Reading efficiency specialists urge that this habit should be eliminated

Finger pointing- similar criticism is made of finger-pointing such as children use to fix their concentration on the word they are deciphering. Again it is true that this can slow down the reading process if the finger points word by word.

Regressions- another reading habit that is often criticized is the occurred of regressive eye movement i.e the eyes moving back to check previous words instead of sweeping steading forward.

23. Culture is the shared knowledge and schemes created by a set of people for perceiving, interpreting, expressing and responding to the social realities around them.